የ1956 የኢትዮጵያና ኢጣሊያን ስምምነት

ባለፈው ሳምንት ቀና አስተሳሰቡን በጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባነው የኢጣሊያን መንግስት በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአክሱሙን ሐውልት እንደወሰደ እንዲቀርለት ለማድረግ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያደርግ ቆይቷል። ይህ ሁኔታም በ1947 ከተዋዋለው ውል በዝርዝርም ሆነ በጠቅላላ መንፈስ የሚቃረን ነበር። እንደሚታወቀው የኢጣሊያ መንግስት በውሉ ውስጥ በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ከኢትዮጵያ የዘረፈውን ሁሉ እንዲመልስ ግዴታ ውስጥ ገብቷል።

የገባውን ግዴታ ከማክበር ይልቅ /ሐውልቱን መመለስ/ በማርች5/1956 ኢትዮጵያን አዲስ ውል ለማስፈረም ያላሰለሰ ጥረቱን ቀጥሎበት በዚህ በአዲሱ ውል መሠረት በአንቀፅ <ሲ> ውስጥ ኢጣሊያ የሐውልቱን መጓጓዣ እስከኔፓልስ ድረስ ብቻ እንደምትከፍል ተመልክቷል።

ይህ የኢጣሊያን ባለሥልጣኖች በእፍረት አንገታቸውን ሲደፉበት የሚገባውና ሐቀኝነት የጎደለው አንቀፅ በቅድሚያ ከተዋዋሉት ውል ጋር የሚቃረን ነበር። እስከ ኔፓልስ ድረስ ብቻ እናጓጉዛለን ብለው የተቀረውን በኢትዮጵያ ላይ መጫን፤ ሌባው መስረቁ አንሶ ለማስመለስ ተሠረራቂው እንዲከፍል ማድረግ ሲሆን የሌባ ዓይነደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ የሚለውን አባባል ያስታውሰናል። በዚያ ላይ ኢትዮጵያ ከዓለም ድሃ አገሮች አንዷና በኢጣሊያ ወረራ የተፈፀመባት መሆኗ መዘንጋት የለበትም።

በዚህ አንቀፅ በኢትዮጵያ በኩል የተገኘ አንድ ነገር ቢኖር ኢጣሊያ ሐውልቱን «ለኢትዮጵያ መመለስ» እንዳለባት ማመኗና «ያለ አንዳች ችግር ከኢጣሊያ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት መንግስት በሚመርጠው መርከብ መጓጓዝ እንደሚችል በግልፅ ተቀምጧል።

የስምምነቱ ጠቅላላ መንፈስ ይህን ይመስላል «ቴሌቪዥንህን ሰርቂያለሁ። ግን አልመልስልህም። ያም ሆነ ይህ ያንተ ንብረት መሆኑ ስለማይካድ በመልካም ሁኔታ ከሳሎኑ ወደ ማድቤት አዛውሬ እጠብቅሃለው። ገንዘብ ስሌለህ መጥተህ ልትወስደው እንደማትችል ደግሞ አሳምሬ አውቃለሁ። ስለዚህ የራስህ ጉዳይ! ገደል መግባት ትችላለህ!»

በሮም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ ፓርላማና የኢጣሊያን ኤምባሲ

1956-1990

በ1947 ዓ.ም. በተደረገው የሰላም ውል መሰረት ኢጣሊያ ሐውልቱን ለመመለስ የገባችውን ቃል አለማክበሯና በ1956 ዓ.ም. ስምምነት በረቀቀ መንገድ የተዘጋጀው ውል በብዙ ጀግና ኢትዮጵያውያን አእምሮ ውስጥ ሲጉላላ ቆይቷል።

በጣሊያን አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ የሐውልቱን መመለስ በመጠየቅ ሰላማዊ ሰልፎችን አድርገዋል። እንዲሁም በአንድ ወቅት በሐውልቱ ላይ «ለመሆኑ ይህ የማን ታሪክ ይመስላችኋል?» የሚል ቃል ፅፈውበታል።

ከዚህ ባላነሰ ሁኔታ የ1970 ዓ.ም. በፀደዩ ወራት በቅድመ-አብዮት ኢትዮጵያ የነበረው ፓርላማ ውሳኔ አሳልፎበት እንዲህ ብሎ ነበር። «የሀገሪቱ ታሪክና ኩራት የሆነው ሐውልት መመለስ ጉዳይ መተው ቀርቶ መዘግየት ስሌለበት ሁሉም የፓርላማው አባላት አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ ተስማምተዋል። በተጨማሪም ለጉዳዩ ክብደት ለመስጠት ለኢጣሊያኖች ወደ ኢትዮድያ እንዳይገቡ ቪዛ በመከልከል፤ የንግድ ልውውጥ ማዕቀብ በመጣልና ዲፕሎማቲካዊ ግንኙነትን በማቋረጥ ርምጃ መውሰድ አለበት ሐውልቱ እስኪመለስ ድረስ ግርማዊ ጃንሆይ ወደ ጣሊያን ሀገር ጉብኝት እንዳያደርጉ»

ይህንን ታሪካዊ ውሳኔ ካሳለፉት መካከል የአሁኑ የአክሱም ሐውልት መመለስ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር ፊታውራሪ አመዴ ለማ ይገኙበታል።

የኢጣሊያን መንግስት በተለመደው እምቢተኝነቱ ይህንን ፓርላሜንታዊ ውሳኔ ለማክበር አልፈቀደም። በሙሶሎኒ ተዘርፎ የመጣለትን ሐውልት ባለማስረከብ ከፋሽስቶች መውደቅ በኋላ የተቋቋመው መንግስት የአንድን ሀገር ሕዝብ ድምፅ እንደባዶ ኳኳታ ከመቁጠርና የፓርላማውንም ውሳኔ ከመናቅ አልተቆጠበም። ቀድሞ በኢትዮጵያ የኢጣሊያ አምባሳደር የነበሩት ሲኞር ፓስቱቺ-ሪጂ በፃፉት «አን ፕሮ ፊሎዴል ንጉሥ ፕሮፌሲዮን ዲፕሎማቲክ» 1990 ውስጥ ለኢጣሊያን ሕዝብ ሲያስረዱ« የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ሐውልቱ ምንነት አንዳችም ዕውቀት የለውም። ስለ ሐውልቱ ፍቅርም ሆነ ባህላዊ ትስስር የለውም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውንማ ምን እንደሆነ እንኳን አያውቀውም» በማለት በአሳፋሪ ሁኔታ ፅፈዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የዚህን አባባል መሠረተ ቢስነት በተግባር አሳይቷል።